በ1957 ሐምሌ ወር (አJuly 1965)

በመጨረሻው አመቴ የተፈሪ መኮንን ሮቨር ስካውቶች ወደ ሐረር ያደረግነው ጉዞ ምንጊዜም የማልረሳው አስደሳች ታሪካዊ ሳምንት ነበር።

እርግጠኛ ወርና ቀናቱ ቅደም ተከትሉ እና አንዳንድ ዝርዝር በጊዜ ብዛት ስለትረሳኝ ይቅርታ እጠይቃለሁ። አብረውኝ ከሄዱት እነንኳን ተዝ የሚሉኝ አባተ ከበደ ፤ ገዝሙ እሸቴ፤ ገለብ ዳፍላ፤ ሰሎሞን በለጠ ፤ አለሙ ከበደ ፤ ሐይለ ሚካአኤል ፤ ግርማ ታደስ ፤ አንድ የቴሌ ልጅ ብቻ ናቸው።

በመጀመሪያው ቀን በባቡር ተሳፍረን ናዝሬትን ፤ አዋሽን ካለፍን በሁዋላ ሚኤሶን ላይ ወረድን ። ራታችንን አብስለን camp fire ሰርተን we are the boys of Teferi Mekonene .............

ዘምረን ፤ ጨፍረን አዳር አደረግን ።

በሁለተኛው ቀን በእግራችን የመኪናውን መንገድ እየተከተልን ስንቃችንን ተሸክመን ሃያ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዘን ተራራውን ወጥተን ደበሶ ከተማ ላይ ድንኳናችንን ተክለን አደርን። ደባሶ ብራዳ ነፋሻ ደጋማ እንደነበረች አስታውሳለሁ።

በሶስተኛው ቀን በእግራችን ዳገት ቁልቁለቱን ወጥተን ወርደን ሚስተር ቦድሪን እየደከመው እኛ ግን እየተደሰትን እየዘፈንን አመሻሹ ላይ ሂርና ከተማ ደረስን። ት/ቤቱ አጠገብ ካንድ ጅረት ዳርቻ ሰፈርን። በነጋታው አካባቢውን ስንቃኝ ግርማ ሞገስ ያላቸው አንድ አዛውንት አገኙን እና ጋዜጠኞች እንደሆንን ቢጠይቁን ተማሪዎች መሆናችንን ነግረናቸውና በርቱ በርቱ ብለው አለፉ። ለካስ ሰውዬው ታላቁ ፊታውራሪ ተክለሐዋሪያት  የሂርና ከተማ መስራች ፤ የሩሲያ ሚሊትሪ አካዳሚ ምሩቅ ፣ በፈረንሳይ የእርሻ ትምህርት የኮሌጅ ምሩቅ ፤ የኢትዮጵያን ሕገመንግስት ያረቀቁ ምሁር ፤ አቮካዶንና ሌሎች ተክሎችን በሃገራችን ያስገቡ መሆናቸውና የነበራቸውን አንገብጋቢ ያገር ፍቅር ያሳለፉትን ውጣውረድ  የእምነታቸውን ፈተናና ሌሎች ለሃገራችን ያበረከቱትን ብዙ አስተዋጻኦ አንብቤ የተረዳሁት ከብዙ ዘመናት በኋላ ነበር።

ከሂርና ተነስተን መንገዳችንን ወድ ቦረዳ ከተማ አቀናን ከዛም ካራሜ ላይ ምሳችንን በላንና ጉዞአችንን ቀጥለን ቆቦ ስንደርስ ከዋናው መንገድ ተገነጥለን 8 ኪሎ ሜትር ወርደን ደደር ከተማንና ገበያውን አይተን ተመለስን ደቦ ላይ አንድ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ አደርን።

ቀጥሎ ጨለንቆን አልፈን ቁልቢ  አደርን። በነጋታው ማልደን ተነስተን ቅዱስ ገብራኤል ቤተ ክርስቲያን ሁላችንም ሚስተር ቦድሪ ሳይቀር አስቀድሰን። ስንጨርስ ከመሃላችን አንዱ አመመውና ወደቀ። እኛም ምናልባት ገብርኤል ያየበት እኛ ያላየነው ሃጢአት ሰርቶ ይሆናል ብለን ስንጨነቅ ፤ ስንጠበብ ወዲያው ተሻለውና መንገዳችንን ቀጠልን።

ቀርሳ ከተማን ፤ የደንገጎን ዳገትን አልፈን አለማያ እርሻ ኮሌጅ ክፍል ተሰጥቶን በሳምንታችን አልጋ ላይ ለመተኛት ለመተኛት በቃን።

የኮሌጁ ተማሪ በነበረው ከኛ ት/ቤት በተመረቀው በሰሎሞን በለጠ አማካይነት ጥሩ መስተንግዶ እየተደረገልን ራታችንን እና ቁርሳችንን ካፊቴራው ውስጥ አይተን፤ ቀምሰን የማናውቀው የሚጣፍጥ ምግብ ሆዳችን እስኪንፋ ድረስ ደጋግመን በላን። እኔም የኮሌጁ ውበትና ጽዳት በተልይ ምግቡም ስለጣመኝ እዚያው ለመመደብ ወሰንኩ። ጉብኝቱን ስንጨርስ በአውቶብስ ሐረር ከተማ ደርስን መድሐኔአለም ት/ቤት አጠገብ ሰፈርን።

የት/ቤቱ ዳሬክተር የኛው የTMS ምሩቅ አደም አብደላ እንደነበር Mr. Baudery ብኩራት ሲነግረን ሁላችንም ደስ አለን። በጥዋት ተነስተን አካባቢውን ስንቃኝ የመንደሩ ልጆች ሲዘፍኑ ሲጫወቱ የሰማሁት ስንኝ እስካሁን ድረስ ትዝ ይለኛል ።

“ አወሮፕላን መጣ  አሃሃ ሰማይ ለሰማይ ፤

እንግዲህ ትማሪ አሃሃ አርፎ አይበላም ወይ።”

ቀኑን ሙሉ ሐረርን ዞርናት። ጀጎልን፤ ሸዋ በርን ፤ ግንቡን መስጊዱን፤ እና ይራስ መኮንን ሃውልትን አየን። ወደ የቀሐስ የጦር አካዳሚ ስንደርስ የፊት ጢማቸውን ፤ ጸጉራቸውን አሳድገው በጥቁር ሻሽ ጠቅልለው የሚሄዱ ወታደሮች በቅሕይውታችን ለመጀመሪያ ጊዜ አየን።

ሴክ የሚባሉ ወታደሮች ለመጀመሪያ ጊዜ አየን። ሲንክ የሚባሉ  ሕንዳውያኖች ፤መኮንኖች ነበሩ። በአካዳሚው mess hall በሚሉት አዳራሽ ውስጥ ምሳ በላን ። ጥራቱ እና ብዛቱ ያለማያ ኮሌጅን ባያክልም ስነ ስራአቱ የማይረሳ ነበር።

እስካሁን ድረስ የማስታውሰው የማልረሳው የአንድ ቆፍጣና እጩ ገጽታና ተክለ ሰውነት ነበር። የዛሬው ሻለቃ አርጋው ሃብታሙ  ያንጊዜ እጩ መኮንን  ምክትል መቶ አለቃ አርጋው እንደ ዘንግ ቀጥ ብሎ ቀጥ ብሎ የተተኮሰ ካኪ ዩኒፎርሙን ለብሶ ገዳዳ ኮፊያውን ደፍቶ ፣ በትረ መኮኑን ከጉያው ሸጉጦ ፣ ኮስተር ብሎ በሚያስገርም ቅልጥፍና ወዲህ ወዲያ ተፍ ተፍ ሲል ግርማ ሞገሱ እጅግ መሳጭ ፣ አስደሳች ፣ አስደናቂ ነበር ። የወታደር ወታደር እንዲህ ነው ወታደር ማለት አልን እያደነቅን። ገዝሙ እሸቴ ወዲያውኑ እኔ እዚህ አካዳሚ መግባት አለብኝ እመዘገባለሁ አለ ። አርቆ አስተዋዩ ገለብ ዳፍላ አርፈህ ተቀመጥ በኋላ እኛኑ ለማስቸገር ነው። እኛ ኮሌጅ ጨርሰን $450 ስንበላ አንተ $250ህን ጨርሰህ አበድሩኝ እያልክ ልታስቸግረን አይድለም? ሁለቱም ተወዳጆች ልጆች ገለብ እና ገዝሙ ዛሬ በህይወት የሉም።